# ለነገ የማይባል የቤት ስራ!

**ሚልዮን ታምሩ 18-04-17**

አገራችን የምትመራበት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት በብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሰፊ ተሳትፎ እና ይሁንታ ፀድቆ የዜጎች እኩልነት፣ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሕገ-መንግሥታዊ ዋስትና እንዲያገኙ አድርጓል፡፡ ሕገ-መንግስቱ በመፈቃቀድ እና እኩልነት ላይ የተሰመሰረተ ብሄራዊ አንድነት እንዲፈጠር ፣ ጠንካራ አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመገንባት የሚያስችል መሰረት የጣለ ታሪካዊ የቃልኪዳን ሰነድ ነው፡፡

በውጤቱም የአገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በጋራ በከፈሉት መስዋዕትነት ብዙህነታቸው ማስተናገድ የሚችል በእኩልነትና መፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት በመመስረት ሰላም፣ ፍትህ ፣ ብልፅግና የሰፈነባት ከድህነት አረንቋ የተላቀቀች አገር የመገንባት ስራ በአንድነት ሆነው እየገነቡ ይገኛሉ፡፡ ለዘመናት ተንሰራፍቶ የነበሩት ኃላቀር ጎታች አስተሳሰቦችና ስር የሰደደ ድህነት መንግስት በተከተላቸው ውጤታማ ፖሊሲዎችና የህዝብ ርብርብ በርካታ ውጤቶች በማህበራዊና ኢኮኖሚዊ ልማት መስኮች ተገኝቷል፡፡

ከልማቱ ጎን ለጎን እኩልም የአገራችን መፃኢ ተስፋ እውን ለማድረግ፣ የልማት ስራው በተጠናከረ መልኩ በማሳደግ የህዝብ ተጠቃሚነት ደረጃ በደረጃ ለማረጋገጥ ከሚያስችሉ ቁልፍ ጉዳዮች መካካል የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ዋነኛው ምሰሶ ነው፡፡ የአገራችን ብዙሃነት በአግባቡ ማስተናገድ የሚችል፣ አገራችን በቀጣይ አስርት ዓመታት ውስጥ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት ተርታ ለማሰለፍ የተቀመጠው ራእይ እውን ለማድረግ እንዲቻል በየጊዜው እያደገና እየዳበረ የሚሄድ የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ሥራ ወሳኝ በመሆኑ በዚህ ረገድ የተለያዩ ስራዎች እየተከናወኑ መሆናቸው ይታወቃል፡፡

ለምሳሌ ያህልም ዜጎች የሚሳተፉባቸውና ውሳኔ የሚሰጥባቸው የአከባቢ ምክርቤቶች መመስረታቸው፣ ጥቅሚን ያስጠብቃሉ ድምፄን ያሰማሉ የሚላቸው ተወካዮቹ በየደረጃው የሚመርጡበት ሕጋዊ አገባብ መፈጠሩ፣ ዜጎች የተለያዩ ሃሳቦች በነፃ የሚያቀርቡበት መድረኮችና አግባብ መኖሩ፣ በተመሳሳይ ዜጎች በተናጠልም ሆነ በቡድን በመደራጀት መብት እና ጥቅሞቻቸው የሚያስከብሩበት አሰራር መዘርጋቱ ፣ የሕግ የበላይነትን ተጠያቂነትና የግልፅነት አሰራር በተቋማት የተደገፉ እንዲሆኑ የተሰሩ ስራዎች ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም በአገራችን ረጂም የታሪክ ሂደት ውስጥ አዲስ የዴሞክራሲ ባህል እና ልምድ የሆነው የመድብለ ፓርቲ ስርዓት(Multi-Party Political System) ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ በማድረግ ህዝብ በነቂስ የተሳተፈባቸው አምስት አገራዊ ምርጫዎች ተካሂዷል፡፡ በዚህም ህዝቡ የዴሞክራሲዊ ስርዓት ግንባታ መሪና ባለቤት መሆኑ ማየት ተችሏል፡፡

የአገራችን ህዝቦች በሕገ-መንግስቱ የተረጋገጠላቸው ዴሞክራሲያዊ መብቶች በመጠቀም ራሳቸው በመረጧቸው ወኪሎች አማካኝነት በየደረጃው ባለው የመንግሥት እርከን ውክልና አገኝተው በአገራዊ ጉዳይ ሙሉ ተሳትፎ እና ውሳኔ የሚሰጡበት አሰራር ተግባራዊ ሁኗል፡፡ ህዝብ በምርጫ በሚሰጠው ይሁንታ የስልጣን ሉኣላዊ ባለቤት መሆኑ አረጋግጧል፡፡ ዜጎች በቀበሌ፣ በወረዳ፣ በዞን፣ በክልል እና ፌዴራል ደረጃ ባሉት ምክርቤቶች ተገቢውን ውክልና በማግኘት ተግባራዊ የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ሥራ በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡

በውጤቱም አገራችን በኢኮኖሚ ልማት እድገት ብቻ ሳይሆን በዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ መስክም በትክክለኛ መንገድ ላይ የምትገኝ መሆኑዋ ከዜጎችዋ በተጨማሪ የውጭ መንግስትታት  ምስክርነት የሰጡበት እውነታ ሁኗል፡፡ የቀድሞ የኣሜሪካ ፕሬዝዳንት ባራክ ኦባማ እ.ኤ.አ በጁላይ 2015 በአገራችን ባደረጉት ይፋዊ የስራ ጉብኝት  ወቅት አገራችን እየገነባችው ያለውን የዴሞክራሲ ስርዓት በተመለከተ ቀጥሎ ያለው ንግግር ማድረጋቸው የሚታወስ ነው፡፡

“We are very mindful of Ethiopia’s history -- the hardships that this country has gone through.  It has been relatively recently in which the constitution that was formed and the elections put forward a democratically elected government. ... there is still more work to do, and I think the Prime Minister is the first to acknowledge that there’s more work to do.” [1]

**ትርጉም፡**

“የኢትዮጵያ ታሪክ በሚገባ እንረዳለን፣ አገሪቷ ያጋጠሙዋት ችግሮች እና ተግዳረቶች ለመፍታት የሄደችበት ረጂም መንገድ በተመሳሳይ እንገነዘባለን፡፡ ኢትዮጵያ ቅርብ በሚባል ግዜ ውስጥ አዲስ ሕገ-መንግስት በስራ ላይ በማዋል የመድበለ ፓርቲ ስርዓት ተግባራዊ አድርጋለች፡፡ ህዝቡ ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ መንግስት የሚመርጥበት ስርዓት መተግበር ችላለች፡፡ አገሪቷ የምትፈልገው የዳበረ የዴሞክራሲ ስርዓት ደረጃ እንድትደርስ ግን በርካታ ሥራ መሰራት እንዳለባቸው ይሰማኛል፡፡” ፕሬዝዳንቱ ከተናገሩት የተወሰደ

ሕገ-መንግስታችን አገራችን የምትመራበት የፌደራላዊና ፓርላሜንታዊ ስርዓት እንዲመሰረት መሰረት ከመጣሉ በተጨማሪ ለምንከተለው የዴሞከራሲ ስርዓት ግንባታ ሂደትም ዋና ምሰሶ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ሕገ-መንግስቱ ከማርቀቅና ማፅደቅ ምእራፍ ጀምሮ እስከ አሁን

1 . White House. (2015, July 27). Remarks by President Obama and Prime Minister Hailemariam Desalegn of Ethiopia in Joint Press Conference. Retrieved April 09, 2017, from https://obamawhitehouse.archives.gov/the-press-office/2015/07/27/remarks-president-obama-and-prime-minister-hailemariam-desalegn-ethiopia

ያሉት እንቅስቃሴዎች ስንመለከት ሕገ-መንግስቱ ለዴሞክራሲ ስርዓት መዳበር ያለው እንድምታና አስተዋፅኦ ማየቱ ጠቃሚ ይሆናል፡፡

1. ሕገ-መንግስቱ በአገራችን ረጂም የታሪክ ምዕራፍ የመጀመሪያ የሚባል የዴሞክራሲ ባህል እንዲያብብ መሰረት የጣለና ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንበታ ሥራ ዋስትናና መሸጋገሪያ ድልድይ መሆኑ፣
2. ሕገ-መንግስቱ በይዘቱ የአገራችን ነባራዊ ሁኔታ በጥልቅ በመተንትን የተዘጋጀ መሆኑና በወቅቱ በአገራችን አሉ የተባሉ የህግና ሕገ-መንግስታዊ ጉዳዮች ሊሂቃን ተረቆ መላ የአገራችን ህዝቦች መክረውብና ተከራክረውበት የፀደቀ መሆኑ በሌላ መልኩ የተለያዩ አማራጭ ሃሰቦች፣ አስተሳሰቦች እና እምነቶች በነፃነት መቅረብ እንደሚችሉ ያሳየ አዲስ ምዕራፍ የከፈተ መሆኑ፣
3. በሕገ-መንግስቱ ረቂቅ ዝግጅት ወቅት የተነሱት ሃሳቦች ቀጥሎም በውይይት ዳብረው በሰነዱ የሰፈሩት አስተሳሰቦችና ፍልስፍናዎች(Principles) የአገራችን ህዝቦች ተስፋ የሚያመለክቱ ተራማጅና ዘመናዊ አስተሳሰቦች የያዙ መሆናቸው፣ ይህም ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታና ባህል መዳበር ሙሉ እውቅና የሰጠ አመቺ ሁኔታ የፈጠረ መሆኑ፣
4. በሕገ-መንግስቱ የተደነገጉት ሰብአዊና ዴሞክራሲዊ መብቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታወቁ የዴሞክራሲ ድንጋጌዎች[2]ና የዘመናዊ ዴምክራሲ መርሆች አካቶ የያዘ መሆኑ ፤ (የዴሞክራሲ መገለጫ መርሆች [3] (the building blocks of modern & representative democracies) በግርጌው ተገልፀዋል፡)
5. በሕገ-መንግስቱ ከሰፈሩት 106 አንቀፆች መካከል ከአንቀፅ 13-44 ወይም ከጠቅላላ ዓንቀፁቹ አንድ ሶስተኛ ገደማ ስለሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የሚደነግጉ መሆናቸው፣ ይህም ዜጎች በማነኛውም አገራዊ ጉዳይ ላይ ባለቤት እና ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ እጅጉን የሚያበረታታ መሆኑ የሚሉ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት እና ባህል ግንባታ ምቹ የሆኑ መደላድሎች ተግባራዊ ለማድረግም ከሕገ-መንግስቱ የመነጬ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብን የተላበሱ ፣ ለሕገ-መንግስቱ እና ሉኣላዊ ለሆነው ህዝብ ውግንና ያለቸው ዴሞክራሲያዊ ተቋማትን በሂደት በመገንባት ላይ የሚገኙ ቢሆንም ተቋማቱ የተሰጣቸውን ኃላፊነት ከመወጣት ኣንፃር እና በተጨባጭ እያከናወኑት ያሉት ስራዎች ስፋት፣ ጥልቀት እና ውጤታማነት ኣንፃር ሲመዘን ገና ብዙ ሥራ እንሚቀር ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡

---

2 . http://www.un.org/en/universal-declaration-human-rights/index.html
3 . The twelve key concepts of modern and representative democracy are: (1) Consent of the Governed; (2) Free Elections; (3) Constitutional Limits; (4) Majority Rule, Minority Rights; (5) Transparency and Accountability; (6) Multiparty System; (7) Economic Freedom; (8) Rule of Law; (9) Human Rights; (10) Freedom of Expression; (11) Freedom of Association; and (12) Freedom of Religion.

በአገራችን የዲሞክራሲ ስርዓት እና ባህል እንዲጠናከር ብሎም እንዲዳብር የሚደረግ ትግል ተግዳረቶቹ በብዛትና በአይነት በርካታ በመሆናቸው በዛ ልክ በየግዜው የሚያቆጠቁጡት የብልሹ አሰራርና ፀረ-ዴሞክራሲ አመለካከት ለማስተካከል የሚጠይቀው ትግል ከባድና የአመራሩ ቁርጠኝነት የህዝቡ ንቁ ተሳታፊነት የሚጠይቅ ነው፡፡

ዴሞክራሲ ለአገራችን የሞት-ሽረት ጉዳይ ነው ስንል መነሳት የሚገባቸው ዓበይት ጉዳዮች በአጭሩ መመለከት አስፈላጊ ይሆናል፡፡

1. አገራችን የበርካታ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦች ህዝቦች መኖሪያ በመሆኗ የህዝቦቿ አብሮነት እና አንድነት እሴት በማስጠበቅ ማነኛውም የውጭ ተፅእኖ፣ ስጋት፣ ጥቃት በመግታት አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ መገንባት የሚቻለው የዳበረ የዴሞክራሲ ስርዓት በመግንባት ሙሉ የህዝብ ተሳትፎ ማረጋገጥ ሲቻል ብቻ መሆኑ፣
2. በዜጎች መካከል እንዲሁም በዜጎች እና መንግስት የሚኖሩ ግንኙነቶች በዴሞክራሲያዊ መርሆች እና አሰራረሮች ተደግፌው ተግባራዊ ማድረግ ለአገራችን ዋስትና ያለው ሰላም እና ቀጣይነት ያለው ልማት ማስፈን አስፈላጊ በመሆኑ፣
3. በሕገ-መንግስቱ የተደነገጉት ዴሞክራሲያዊ መብቶች በተለይም የዜጎችን ያልተገደበ የአመለከካትና ሃሳብን በነፃ የመግለፅ መብት ፣ ለዴሞክራሲ ሥርዓት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች፣ ሀሳቦችና አመለካከቶች በነፃ መንሸራሸር፣ የመገናኛ ብዙሃን በንቃት ተሳትፎ ማድረግ ፣ የሲቪክ ማሕበራት መጠናከር፣ የተለያዩ አስተያየቶች የማስተናገድና ልዩነት በውይይት የማጥበብ አቅም ማዳበር ለአገራችን ዘላቂ ልማት እና ሰላም መረጋገጥ ከፍተኛ ሚና ያለው መሆኑ፣
4. ህዝቡ የሚያነሳቻው ጥያቄዎች በወቅቱ ምላሽ እና መፍትሄ እንዲያገኝ የዴሞክራሲ ስርዓትና ባህልና መዳበር የዴሞክራሲ ተቋማት አቅም ማደግ እጅጉ አስፈላጊ መሆኑ፣
5. ኃላፊነታቸው በአግባቡ የማይወጡ ፣ የህዝብን አመኔታና ያጡ አካላት ተጠያቂ ለማድረግ የዴሞክራሲ ስርዓት ማዕቀፍ ወሳኝ መሆኑ የሚሉ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በአሁኑ ወቅት መላው የአገራችን ህዝቦች ፊታቸው ሙሉ በሙሉ ወደ ልማት በማዞር የፀረ ድህነት ትግሉ ከመቼውም ግዜ በበለጠ ሁኔታ አጠናክረው ቀጥለዋል፡፡ አገራችን ለረጅም ዘመናት ከኖረችበት አስከፊ ድህነትና ኋላቀርነት በመላቀቅ በአዲስ የለውጥና ዕድገት ጉዞ ላይ ትገኛለች፡፡ ይህን ፈጣን ግስጋሴ ወደ ከፍ ያለ ደረጃ ለማሸጋገርና ለማስቀጠል የህዝብ ምክርቤቶች፣ የመገናኛ ብዙሃን፣ የሲቪክ ማህበራትና የፓለቲካ ፓርቲ አባላት እንዲሁም በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሰፊ ርብርብ እና ተግባራዊ እንቅስቃሴ ይጠይቃል፡፡

በተለይም በየደረጃው ያሉ ምክርቤቶች ሰፊ የህዝብ ተሳትፎ የሚረጋገጥባቸው፣ አገራዊ ጉዳይ በተመለከተ ውሳኔ የሚሰጥባቸው፣ ለልማት የሚውለው በጀት የሚፀድቅበትና አፈፃፀሙ ክትትል የሚደረግበት፣ አስፈፃሚ አካል የሚያቀርበው ሪፖርት ማዳማመጥ ብቻ ሳይሆን የሚተችበትና በጥልቀት የሚታይበት (scrutiny)፣ ለመንግስት ስራ ኃላፊነት የሚቀርቡትን ተሿሚዎች በአግባቡ የመመርመር ሃላፊነት ያለበት በአጠቃላይ ከህዝብ የሚቀርቡትን ጉዳዮች በመፈተሽ ብልሹ አሰራሮችና ብልሹ አመራረሮች በመታገል ረገድ የማይተካ ቁልፍ ሚናና ግዴታ አላቸው፡፡

በምክርቤቶቻችን የሚወጡት ሕጎች ከመፅደቃቸው በፊት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የተለያዩ የምክክር መድረክ መንገዶች በመጠቀም ለምሳሌ የባለሙያ አስተያየቶች(Expert opinion) በማሰባሰብ፣ የህዝብ ምክክር መድረኮች(Public Consultations) በማዘጋጀት በመረጃ የተደገፈ በቂ ክርክር ተደርጎባቸው እንዲፀድቁ ማድረግ ለአዋጆቹ ተፈፃሚነትና ውጤታማነት፣ ለተቋም አቅም ግንባታ ስራዎች፣ የህዝብን ተሳትፎና ተአማኒነት በማረጋገጥ ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡

በተመሳሳይ መገናኛ ብዙሃን ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ከፍተኛ እና ቁልፍ መሆኑ በመገንዘብ አሁን ካለው ጥረት በበለጠ ወደ ላቀ የመረጃና ዘጋባ አቀራረብና(Investigative Journalism )[4] ማደግ ይኖርበታል፡፡ በተለይም እንደ አገራችን በመሳሰሉ አዳጊ ኢኮኖሚና በርካታ ወጣት ሃይል ያላቸው አገራት የመገናኛ ብዙሃን የተለያዩ ሃሳቦች የሚንሸረሸርባቸው፣ በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ዙሪያ ምክንያታዊ ክርክሮች የሚደረግባቸው፣ ወቅታዊ መረጃና ዘጋባ ለህዝብን በማድረስ ለማህበረሰባዊ ለውጥ ተግተው የሚንቀሳቀሱ ተቋማት መሆን ይኖርባቸዋል የሚል አስተያየት እየጨመረ መጥቷል፡፡

ለምን? እንዴት? የሚል ተመራማሪ እና ጠያቂ ትውልድ ለዘመናዊ አገር ግንባታ መሰረት ነው፡፡ የህዝብ ምክርቤቶችም በተመሳሳይ በሕገ-መንግስቱ እና መራጩ ህዝብ የተሳጣቸው እምነትና ኃላፊነት መሰረት በማድረግ አስፈጻሚው አካል በደንብ ሊጠይቁት፣ ሊቆጣጠሩትና ሊገመግሙት ይገባል፡፡

ዜጎች፣ በየደረጃው ያለው የመንግስት አካል፣ የምክርቤት አባላት፣ መገናኛ ብዙሃን፣ ሲቪክ ማህበራት፣ የፓለቲካ ፓርቲ አባላት በሙሉ ሕገ-መንግስታዊ መርሆዎቹ እና ድንጋጌዎቹ በማክበርና በማስከበር፣ እንዲሁም ሕገ መንግሥታዊ መብቶቻቸውን በመጠቀም የአገራችን ሕዳሴ ለማረጋገጥ በላቀ ተሳትፎ የበኩላቸውን ድርሻ መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡

---

4 . An investigative journalist is a man or woman(institution) whose profession it is to discover the truth and to identify lapses from it in whatever media maybe available.

መልካም አስተዳደር ለማስፈን ወሳኝ የሆነውን የህዝብ ተሳትፎ እንዲናጠናከር፣ የሃሳብ ልዩነትን የማስተናገድ ልዩነትን በውይይት የማጥበብ አቅም እንዲዳብር እና የሃሳብ ክርክር ባህል እንዲያብብ የፀረ-ዴምክራሲ አስተሳሰብ ልንታገል ይገባል፡፡

አገራችን ሉአላዊነትዋ ከውጭ ወራሪ ሃይል በድል አድራጊነት መጠበቅ መቻልዋ በዓለም ታሪክ ልዩ ክብር እንድታገኝ አስችሏታል፡፡ ለዘመናት የማይታሰብ የነበረውን አይቻልም አስተሳሰብ በመሰበር የአባይ ወንዝ በመገደብ ለሃይል ምንጭ ለማዋል ቀን ተሌሊት እየሰራች ትገኛለች፡፡ በቅርቡም የራሷ ሳትላይት ወደ ህዋ ለማምጠቅ በዝግጅት ላይ ትገኛለች፡፡

የአገራችን ህዳሴ ጉዞ ይበልጥ ለማፋጠን፣ የህዝባችን ሁለንተናዊ አቅም ተሳትፎ ለማሳደግና የዳበር የዴሞክራሲ ባህል ባለቤቶች እንድንሆን የህግ የበላይነትን የተጠያቂነት አሰራርን የማጠናከር ቁልፍ ሥራ ለነገ የማይበል የቤት ሥራ በመሆኑ እንያንዳንዱ ዜጋ ይህንኑ ተግንዝቦ ተሳትፎና ርብርብ ሊያደርግ ይገባል፡፡

ቸር እንሰንብት!